# እስቲ በልማቱ አንጣላ

ተኮላ መኮንን
ዳላስ
4-23-2010

የዘመናት ትግል ስሌት የወጣት ሽማግሌ ደም፡
ከየት ተብሎ ሲተረክ፡- በማን ተብሎ ሲገመገም።
ሁሉም ድርሻውን ሲያሞጋግስ ያልተስማማውን ሲያጥላል፤
ያለፈውን በትዝታ መጭውን በይሆናል እያሰላ፤
ይኽ ወንበር መጥፎ ነገር ከግራ ቀኝ ሰው አባላ።
እንደ ደጀ ሰላም ሰሞነኛ ባግዳሚ ወንበር ተጋደለ፡
ስሉስ የቀናው በጡንቻ ያልሆነለት ሽለላውን ቀጠለ።
ቆይ ግድ የለም ሆነ መሃላው፡
ባለፈ ጋቢ ተሸፋፍኖ መጭው ሁሉ አስጠላው።
ቅኝቱንም አልቀየረ በነበረበት ቆሞ፡
ማንጎራጎር ብቻ ቀረው ብስጭቱን አስታሞ።
ኧረ እስቲ ዞር ብለን አይተን ማርጀታችንን እንቀበል፡
የጦርነት ከበሮ ይቅርና የሰላም ችግኝ እንትከል።
ቃታ ሳይሆን ማረሻ፡
ጦር ሳይሆን መዶሻ፡፡
እንጀራና አንባሻ ለተራበው፡ እንስጠው፡
ማቅና ዝተት አናልብሰው፡
በመሰለው ይቀናጅ በዘር ቋጠሮ አናፍነው።
እኔማ አማራነት አይገባኝ ኢትዮጵያዊነት ተዋህዶኝ፡
እንደ ባለሞያ ጥበብ የሕብረ ሕዝቡ ቀለም አስጊጦኝ።
የኦሮሞ አካል መሆኔ አኩርቶኝ፡
የትግራይ ታሪኬ አንጠራርቶኝ፡
የወሎ የእምነት ሃውልት አስደስቶኝ፡
የባሌው ሸህ ሁሴን ናፍቆኝ፡
ሐረረ ድሬ ውል ብሎኝ፡
ጎንደር ፋሲለደስ ታውሶኝ፡
የማርቆስ የባህርዳር ትዝታ ተብትቦኝ፡
የሰሜን ሸዋ እድገቴ ጋርዶኝ፡
የሲዳማ የወላይታ የጉጂ ሕብረ ቀለም አስደስቶኝ፡
የጉራጌ ታታሪነት የዶርዜ ጥበብ አስቀንቶኝ፡
የወለጋ የቢል ሻንጉል ፈገግታ ታይቶኝ፡
ያኑሲ ጉድሮ ያፋር ልበሙሉነት ተጠናውቶኝ፡
እንዴት ብዬ ልታጠር ኢትዮጵያነት ተላብሶኝ።
የዓለም ጭቁን ሕዝብ አንድ ነው ባልኩበት ፡
ታጥፌ ጎጥ ቀበሌ አልልበት ።
ሕዝብ ድንበር የለውም ብዬ ዛሬም በእምነቴ እጸናለሁ፡
የማይስማሙትን አክብሬ የራሴን ይገቼ እሞ ታለሁ።

ለልማቱ ግን ልሰለፍ አቅም ጉልበቴ በቻለው፡
የኔ ውሱን ድጎማ እረሃብተኛውን ካቃመሰው፡
ድር ቢያብር እንዲሉ የጤና ችግሩን ከቀረፈው፡
የተሰበሰበ ተጠራቅሞ መሃይምነቱን ካስገፈፈው፡
መታገል ማለት መጨራረስ ነው የሚል ማን ነው?
ድህነት የሚጠፋ እንጂ አይደለም ቋሚ ነቀርሳ፡
ካመንበት ተሰባስበን እረሃብን ለማጥፋት እንነሳ።
ፈረነጆች ከመቀበል ይልቅ መስጠት ያስደስታል እያሉ፡
ለማን እንደለገሱ ስም ከመጥራት ይቆጠባሉ።
እናም ማን ተመሰገነ ማ፡
ሥራው ይጀመርና መንደር ቀበሌው ይልማ፡
በፖለቲካው እንፋጭ የትግል መስመር እናስላ፡
ወንድሞች በቅን ካሰብነው በልማቱስ አንጣላ፡
ለመታገሉም ጤነኛ እንዲሆን ሳይሳቀቅ ጠግቦ ይብላ።

ለመልእክት እንዲያመች የተጻፈውን አንብቦ እንዲረዳ፡
ፊደል እንላከለት የተጣራ ውሃም ይቅዳ።
ወንድሞችና እህቶች ማን ይመስገን ማ፡
ምን መጥፎ ነገር ይኖርበታል መንደር ቀበሌው ቢለማ።